# ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክስዮን ማህበር
## መመስረቻ ጽሁፍ

እኛ ስማችን፣ ዜግነታችንና አድራሻችን ከዚህ በታች በአንቀጽ 1 ስር የተመለከተው መስራች አባሎች በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረትና ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ ድርጅቶች ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 40/1988 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች እንዲሁም በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍና የዚህ አካል በሆነው የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ድርጅት አክስዮን ማህበር (ከዚህ በታች ማህበሩ) ተብሎ የሚጠራውን አቋቁመናል።

**አንቀጽ 1**

**የመስራቾች ስም፤ ዜግነት፤ አድራሻና የአክስዮን ድልድል**

የመስራቾች ስም፣ ዜግነት፣ አድራሻና የአክስዮን ድልድል ከዚህ እንደሚከተለው ነው:-

| ተ.ቁ | ሥም | ዜግነት | አድራሻ | የአክስዮን ብዛት | የአንድ አክስዮን ዋጋ ብር | የተፈረመ ዋጋ ብር | ጠቅላላ የተከፈለ ብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | ኢትዮጵያዊ | ወ. 11 ቀ. 19 አ.አ. የቤ.ቁ. 703 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 2. | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | " | ወ. 17 ቀ. 23 አ.አ. የቤ.ቁ. 2111 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 3. | አቶ ኃ/ማርያም ኃ/መስቀል ባንተረሳሁ | " | ወ. 17 ቀ. 20 አ.አ. የቤ.ቁ. 4026 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 4. | አቶ ግርማ ባንቲወሰን አይነቱ | " | ወ. 17 ቀ. 19 አ.አ. የቤ.ቁ. 669 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 5. | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | " | ወ. 18 ቀ. 41 አ.አ. የቤ.ቁ. 379 | 64 | 1,000 | 64,000 | 32,000 |
| 6. | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መከተ | " | ወ. 16 ቀ. 10 አ.አ. የቤ.ቁ. 092 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 7. | ወ/ሮ ለበሰች ፀጋ ባለህ | " | ወ. 16 ቀ. 10 አ.አ. የቤ.ቁ. 100 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 8. | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ዌ/ጊዮርጊስ | " | ወ. 19 ቀ. 55 አ.አ. የቤ.ቁ. 415 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 9. | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | " | ወ. 2 ቀ. 05 ሻሸመኔ የቤ.ቁ.411 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 10. | አቶ ኃይሌ ከፈኔ ጆሮ | " | ወ. 24 ቀ. 15 አ.አ. የቤ.ቁ. 873 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 11. | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | " | ወ. 17 ቀ. 14 አ.አ. የቤ.ቁ. 399 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 12. | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | " | ወ. 14 ቀ. 13 አ.አ. የቤ.ቁ. 967 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 13. | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰማነው | " | ወ. 23 ቀ. 12 አ.አ. የቤ.ቁ. 1171 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 14. | ሲ/ር መሰረት ሺፈራው ይብራሁ | " | ወ. 28 ቀ. 01 አ.አ. የቤ.ቁ. 616 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| 15. | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | " | ወ. 2 ቀ. 13 አ.አ. የቤ.ቁ. 184 | 24 | 1,000 | 24,000 | 12,000 |
| | ድምር | | | 400 | | 400,000 | 200,000 |

## አንቀጽ 2

## የማህበሩ ስም

የማህበሩ መጠሪያ ስም "ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክስዮን ማህበር" ነው።

## አንቀጽ 3

## የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት

የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ወረዳ 18 ቀበሌ 41 የቤት ቁጥር 379 ሆኖ አስራ አንድ ወኪል ጽ/ቤቶችን በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ፤ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች በመክፈት ስራውን የሚጀምር ሲሆን ሌሎች ወኪል ጽ/ቤቶችን እንደአስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች ሊከፍት ይችላል።

## አንቀጽ 4

## የማህበሩ ዓላማዎች

ሀ) በአዋጅ ቁጥር 40/1988 መሠረት በአነስተኛ የምርትና የአገልግሎት ዘርፎች ለተሰማሩና አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰዎች በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ብድር መስጠት፤

ለ) የቁጠባ ገንዘብ እንዲሁም በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈልና በጊዜ ገደብ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፤

ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ ተከፋይ የሚሆኑ የሀዋላ ወረቀቶችን ማውጣትና መቀበል፤

መ) ገቢ ማስገኘት የሚችሉ እንደ ግምጃ ቤት ሰነድ የመሳሰሉትን የንግድ ወረቀቶች መግዛት፤

ሠ) በንብረቱ ዋስትና ወይም በሌላ አኳኋን ለድርጅቱ ሥራ የሚውል ገንዘብ መበደር፤

ረ) የተቋሙን ሥራ ለማስፋፋት የሚገኘውን ትርፍ መልሶ ስራ ላይ ማዋል፤

ሰ) ለደንበኞች የመረጃና የቴክኒክ እገዛ በመስጠት የአነስተኛ ገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች እንዲስፋፉ ማድረግ፤

ሸ) የምክር፣ የቴክኒክ እገዛና አገልግሎት የመስጠትና የተጠቃሚዎችን የአስተዳደር ብቃት ማሳደግ፤

ቀ) ከማህበርተኛ ድርጅቶች ጋር በሚደረግ ስምምነት በጥላ ድርጅትነቱ የብድርና የቁጠባ ፕሮገዞዎችን መረከብ እና ወይም ፈንዱን ማስተዳደር፤

በ) በአነስተኛ ብድር አቅርቦት የሚሰማሩ ድርጅቶች በተለምዶ የሚያከናውኑአቸውን ተግባራት ሁሉ ማከናወን፤

## አንቀጽ 5

### ካፒታል

ሀ. የአክስዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ዋጋ ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ.) ነው።
ለ. የአክስዮን ማህበሩ የተከፈለ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ.) ነው።
ሐ. የአክስዮን ማህበሩ ካፒታል በንግዱ ህግ (commercial code) አንቀጽ 464 መሰረት የሚጨምር ይሆናል።

## አንቀጽ 6

### የአክስዮን ብዛትና የአንዱ አክስዮን ዋጋ

እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 ዋጋ ያላቸው አራት መቶ (400) አክስዮኖች አሉት። አክስዮኖች በሙሉ በአባላት ስም ተመዝግበው ቁጥር የተሰጣቸው ናቸው። አክስዮኖች በሙሉ እኩል ዋጋ አላቸው።

## አንቀጽ 7

### የማህበሩ ትርፍ ክፍፍል

ሀ. ቦርዱ በየሂሳብ አመቱ መጨረሻ የማህበሩን ንብረትና ዕዳ የሚያሳይ የገንዘብ አቋም ዘገባ ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል።
ለ. የማህበሩን ዓመታዊ የገንዘብ አቋም የሚያሳዩ ሰነዶች፣ የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ የንብረት ቆጠራና የኦዲተሮች ዘገባ በማህበሩ መዝገብ ላይ ለተመዘገቡ ባለአክስዮኖች ከመደበኛው ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ አሥራ አምስት ቀናት ቀደም ብሎ በሪኮማንዴ ደብዳቤ ይላካል።
ሐ. ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ 10% (አሥር በመቶው) በየዓመቱ ወደ ማህበሩ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ የሚተላለፍ ሲሆን ይኸውም የማህበሩ ካፒታል 20% እስኪሆን ድረስ የሚቀጥል ይሆናል።
መ. ቀሪው ትርፍ ለባለ አክስዮኖች የሚከፋፈል ሳይሆን መልሶ ለማህበሩ ተግባራት ማስፋፊያና ማሳደጊያ የሚውል ይሆናል።

## አንቀጽ 8

### የማህበሩ የአስተዳደር አካላት

የማህበሩ የአስተዳደር አካላት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፤
ለ. የዲሬክተሮች ቦርድ፤
ሐ. የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ እና
መ. ኦዲተሮች።

የፌዴራል ... ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት

## አንቀጽ 9

## የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በማናቸውም የማህበሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው።

## አንቀጽ 10

## የዲሬክተሮች ቦርድ

ሀ. ማህበሩ የሚተዳደረው በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጥ ዲሬክተሮች ቦርድ ይሆናል።

ለ. የሚከተሉት የመጀመሪያዎቹ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ናቸው።

1 አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ በአቶ ጌታቸው ወርቁ በመወከል
2 አቶ ሀይለማርያም ሀይለመስቀል
3 አቶ ግርማ ባንቲወሰን
4 ወ/ሮ ለበሰች ፀጋ
5 ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ

## አንቀጽ 11

## የዲሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር

1. የዲሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ፣ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባዔው በሚሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት ሥራውን የማከናወን ግዴታ ያለበት ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ) የማህበሩን አስተዳደር ይቆጣጠራል፤

ለ) ዋና ሥራ አስኪያጁን ይሾማል፣ ከስራ ያሰናብታል፣ እና ሥራውን/ዋን ይቆጣጠራል፤

ሐ) የባለ አክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማህበሩን ስራ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

መ) የቅርንጫፍ ወይም ወኪል ጽ/ቤቶችን መክፈት ይፈቅዳል፤

ሠ) ማህበሩ የኦፕሬሽን ፣ የፋይናንስ እና የሰራተኛ አስተዳደር ፖሊሲ/እንዲኖረው ያደርጋል፤

ረ) የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዥ እና ሽያጭ ይፈቅዳል፤

ሰ) ስለ ማህበሩ ገንዘብ አጠቃቀም ለጠቅላላ ጉባዔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሸ) ከሌሎች አበዳሪ ድርጅቶች ማህበሩ ገንዘብ እንዲበደር ይፈቅዳል፣ እና

ቀ) ሌሎች በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል።

አንቀጽ 12

የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ

የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ የማህበሩን ዓላማ ለማስፈፀም ይችል ዘንድ የሚከተለው ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል/ይኖራታል:-

1. በማህበሩ ቦርድ በፀደቀ ፖሊሲ መሰረት የማህበሩን አጠቃላይ ሥራ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፣ ያቀዳል፣ ያስተዳድራል።

2. በማህበሩ ደንብና የሰራተኞች ማስተዳደሪያ መሰረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፣ ያስተዳድራል፣ በሥራ ሁኔታዎች፣ በዕድገታቸውና በደመወዛቸው ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

3. በማህበሩ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል።

4. በማናቸውም ሦስተኛ ወገን ወይም ፍ/ቤት ፊት ማህበሩን ይወክላል፣ ወይም ጠበቃ ይሾማል።

5. የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለቦርዱ ያቀርባል፤

6. በዲሬክተሮች ቦርድ የሚሰጠውን ሌሎች ጉዳዮችን ያከናውናል፣ ወይም ከሥራቸው ጋር አግባብነት ያለውን ማናቸውንም ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል።

አንቀጽ 13

ኦዲተር

1. ማህበሩ በባለ አክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሚሰየም ኦዲተር ይኖረዋል። ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በንግድ ሕግ ቁጥር 373-380 መሰረት የሚገዛ ይሆናል።

2. የኦዲተሮች ቁጥርና ክፍያቸው በባለ አክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰን ይሆናል።

3. በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ኦዲተር ለሁለት አመት ያገለግላል።

አንቀጽ 14

ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ በንግድ ሕጉ ቁጥር 495 ስር በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት በማንኛውም ጊዜ ሊፈርስ ይችላል።

## አንቀጽ 15

ይህ የመመስረቻ ጽሁፍ ተግባራዊ የሚሆነው ማህበሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

የማህበሩ መሥራች አባላት ይህን መተዳደሪያ ደንብ ዛሬ መጋቢት 28 ቀን 1991 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውስጥ አንብበን አጽድቀናል።

| ተ.ቁ | ባለአክስዮን | የተወካይ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | | 27/1/92 |
| 2. | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | | 02/02/92 |
| 3. | አቶ ኃ/ማርያም ኃ/መስቀል ባንተረሳሁ | አቶ ኃ/ማርያም ኃ/መስቀል ባንተረሳሁ | | 25/01/92 |
| 4. | አቶ ግርማ ባንቲወሰን አይነቱ | አቶ ግርማ ባንቲወሰን አይነቱ | | 04/02/92 |
| 5. | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወልደማርያም | | 10-02-92 |
| 6. | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መከተ | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መከተ | | 25/1/99 |
| 7. | ወ/ሮ ለበሰች ፀጋ ባለህ | ወ/ሮ ለበሰች ፀጋ ባለህ | | 24/1/92 |
| 8. | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | | 25/1/92 |
| 9. | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | | 4/2/92 |
| 10. | አቶ ኃይሌ ከፊኔ ጆሮ | አቶ ኃይሌ ከፊኔ ጆሮ | | 4/2/92 |
| 11. | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | | 25/1/92 |
| 12. | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | | 24/1/92 |
| 13. | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | | 24/01/92 |
| 14. | ሲ/ር መሰረት ሺፈራው ይብራሁ | ሲ/ር መሰረት ሺፈራው ይብራሁ | | 25/01/92 |
| 15. | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | | 25/01/92 |

በክልል 14 መስተዳድር
የዞን 3 ፋይናንስ ጽ/ቤት የታምብር ቀረጥ ማረጋገጫ
ማኅተም
የተከፈለበት ምክንያት መተዳደሪያ ደንብ
የገንዘብ ልክ ብር 355—
በፊደል
ወይም ብር የገ ምድ ተገኝቷል
የደረሰኝ ቁጥር 475245
9/2 ቀን 19 92 ዓ.ም.
የቴምብር ቀረጥ ሠራተኛ አስፈጻሚ
ስም ገ/ጻድቃን ...
ፊርማ

# ፒስ አነስተኛ የገንዘብ ተቋም አክስዮን ማህበር
## የመተዳደሪያ ደንብ

**አንቀጽ 1**

**ጠቅላላ**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶችን ፈቃድ ለመስጠትና ሥራቸውን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ 40/88 እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሰረት የተቀረፀና የማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ አካል ሆኖ ማህበሩ የሚገዛበት ደንብ ነው።

**አንቀጽ 2**

**የአክስዮኖች ምዝገበ**

የማህበሩ አክስዮኖች በሙሉ በማህበሩ መዝገብ ይመዘገባሉ። ምዝገባውም በእያንዳንዱ ባለአክስዮን የተከፈለውንና የተፈረመውን አክስዮን መጠን የሚገልጽ ይሆናል።

**አንቀጽ 3**

**የአክስዮኖች መተላለፍ**

1. የአክስዮኖች ባለቤትነት የሚረጋገጠው የአክስዮኖች መዝገብ በሚያመለክተው መሰረት ይሆናል።

2. ከማህበሩ መሥራቾች ውጪ አክስዮኖችን ለማስተላለፍ የሚቻለው የዲሬክተሮች ቦርድ ጠቅላላ ስምምነት ሲገኝ ነው።

3. ባለአክስዮኖች በማንኛውም ሁኔታ የአክስዮኖችን ንብረትነት ከዚህ የሚገኘውንም ትርፍ ለግል ጥቅም የማዋል መብታቸውን ለመተዋቸው የማይታጠፍ ስምምነት አድርገዋል። ሆኖም ኩባንያው የተቋቋመበትን ዓላማ ለሚደግፍ ድርጅት ወይም ግለሰብ አክስዮናቸውን በስጦታ መልክ የማስተላለፍ መብታቸው የተጠበቀ ነው።

4. በመሥራቾች የተያዙት ወደፊትም የሚሸጡት አክስዮኖች በሙሉ ለማህበሩ ዓላማዎች ማስፋፊያ እንጂ ለማንም ሦስተኛ ወገን በሌላ መልኩ የሚተላለፉ ወይም የሚሰጡ አይሆኑም።

**አንቀጽ 4**

**የባለአክስዮኖች መዝገብ**

1. የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ የባለአክስዮኖችን መዝገብ በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ ያደርጋል። መዝገቡም የንግድ ሕጉ፤ የመመሥረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንቡ የሚጠይቃቸውን ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ ይሆናል።

2. በመዝገቡ ውስጥ ጉድለት መኖሩ ከታወቀ የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጉድለቱ መኖሩን ባወቀ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲስተካከል ያደርጋል።

## አንቀጽ 5

### እንደራሴነት

1. ማንኛውም ባለአክስዮን በባለአክስዮኖች ጉባዔ ላይ የሚወክለው እንደራሴ የመሾም መብት አለው።

2. ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እንደራሴ ከባለአክስዮኑ የሚኖረው የተለየ መብትና ግዴታ የለም።

3. የእንደራሴው የውክልና ሥልጣን ባለአክስዮኖች ባሉበት በፅሁፍ ሆኖ የተፈረመ እና ቀን የተጻፈበት መሆን አለበት።

## አንቀጽ 6

### የጠቅላላ ጉባዔ ስልጣን

1. የማህበሩን የዲሬክተሮች ቦርድ፣ እና ኦዲተር መሾም፣ መሻር እና ክፍያቸውን መወሰን፤

2. የኩባንያውን የዲሬክተሮች ቦርድ እና የኦዲተሮችን ዘገባ መመርመርና ማጽደቅ፤

3. የዲሬክተሮች ቦርድን የውሳኔ ሀሳብ ከገመገመ በኋላ ፖሊሲዎችን መቀየስ፤

4. የማህበሩን መመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ ማጽደቅና ማሻሻል፤

5. የማህበሩን ዓመታዊ ፕላንና በጀት ማጽደቅ፤

6. የጠቅላላ ጉባዔው የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በንግድ ህጉ መሰረት ይሆናል።

## አንቀጽ 7

### የዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን

የዲሬክተሮች ቦርድ ከጠቅላላው ጉባዔ ቀጥሎ ከፍተኛው የማህበሩ አመራር አካል ነው። የዲሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማኅበሩ መመሥረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባዔው የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት የማክናወን ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 8

### የማህበሩ ሥራ አመራር

1. የማህበሩ ሥራ አመራር የሚከናወነው በዋናው ሥራ አስኪያጅ ሲሆን፣ የሚሾመው ተግባሩና የአገልግሎት ክፍያው የሚወሰነው በቦርዱ ይሆናል።

2. ዋና ሥራ አስኪያጅ በሕግ፣ በማህበሩ መመሥረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን እና ከዲሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የማህበሩን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፤ ያስተዳድራል። እንዲሁም የማህበሩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚጠቅሙ ማናቸውንም ተግባራት ይፈጽማል።

3. ዋናው ሥራ አስኪያጅ በዲሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡ ሌሎች ኃላፊነቶች እና ተግባሮች ይኖሩታል።

<u>አንቀጽ 9</u>

<u>ስብሰባ</u>

1. የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ ከስብሰባው አጀንዳ ጋር ከስብሰባው 15 ቀን በፊት ለባለአክስዮኖች ይላክላቸዋል።

2. ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ባለአክስዮኖች ውስጥ ከግማሽ በላይ ስምምነት ካገኘ የጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ ሊሻሻል ይችላል።

<u>አንቀጽ 10</u>

<u>የስብሰባ ሥነ ስርዓት</u>

1. የዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ ሌላ ለጊዜው የሚመረጥ ሰው ማንኛውንም ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራል።

2. ጉባዔው የስብሰባውን ጸሐፊ ይመርጣል፤ ጸሐፊ ከባለአክስዮኖች ውጭ መምረጥ ይቻላል።

3. የባለአክስዮኖች ስም፣ የድምጽ መስጠት መብት እና በስብሰባው የተገኘ እንደራሴ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ መዝገብ ይመዘገባል።

4. የስብሰባው ውይይቶች እና ውሳኔዎች በንግድ ሕጉ ቁጥር 411 እና 412 መሰረት በጽሁፍ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ 11</u>

<u>የዲሬክተሮች ቦርድ ጸሐፊ</u>

1. የዲሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ በቦርዱ ይመረጣል/ትመረጣለች።

2. የቦርዱ ፀሐፊ የቦርዱን ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ትይዛለች/ይይዛል፤ ሰነዶችንም ይይዛል/ትይዛለች።

<u>አንቀጽ 12</u>

<u>የዲሬክተሮች መሾምና መሻር</u>

1. አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ ይሾማሉ።

2. የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ጊዜ ሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም ለተከታታይ አንድ የሥራ ጊዜ ብቻ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ።

3. የቦርድ አባላት በመመሥረቻ ደንብ አንቀጽ 11 እና በመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 15 መሠረት የተጣለባቸውን ተግባር ካልተወጡ ከሥራቸው ይሰናበታሉ።

## አንቀጽ 13

## የዳሬክተሮች ምዝገባ

የዳሬክተሮች የሥራ እና የሕይወት ታሪክ፤ ሙያቸውን እንዲሁም በሌሎች ኩባንያዎች ውስጥ የነበራቸውን የአስተዳዳሪነት ሥራ የሚያሳይ መዝገብ ማህበሩ በዋናው ጽ/ቤት ያስቀምጣል። ዳሬክተሩ ኩባንያ ከሆነ የኩባንያው ስም እና የዋና ጽ/ቤት አድራሻ መገለጽ አለበት።

## አንቀጽ 14

## የዳሬክተሮች የአገልግሎት ክፍያ

የዳሬክተሮች የአገልግሎት ክፊያ መጠን እና አከፋፈሉ በጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል። ሆኖም ኩባንያው እንዲህ አይነቱን ክፍያ መፈጸም የሚጀምረው ትርፋማ መሆን ሲጀምር ነው።

## አንቀጽ 15

## የዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

1. በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ይካሄዳል።

2. የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ከቦርድ አባላት የሚመረጥ ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑ ሁለት ዓመት ነው።

3. በማናቸውም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር አስቸኳይ ልዩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

4. በዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ የሚተላለፍ ውሳኔ በንግድ ሕጉ ቁጥር 358 መሰረት ተመዝግቦ ይቀመጣል።

5. በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከዳሬክተሮች ቦርድ አባል ውስጥ አብዛኞቹ ካልተገኙ የፀና ውሳኔ ሊተላለፍ አይቻልም። ውሳኔዎች የሚያልፉት ፍጹም በሆነ የድምጽ ብልጫ ነው።

6. የቦርድ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ መልክ ተጽፈው በሁሉም የቦርድ አባላት ከተፈረሙ በኋላ በሰነድነት ይቀመጣሉ።

## አንቀጽ 16

## የዳሬክተሮች ለማህበሩ ተጠያቂነት

1. ዳሬክተሮች ከአንድ ወኪል በሚጠበቅ ጠንቃቃ ቅንነት በሕጉ በመመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንቡ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት የተሰጣቸውን ተግባሮች መፈጸም አለባቸው።

2. ዳሬክተሮች ግዴታቸውን ባለመወጣት በማህበሩ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት በአንድነት እና በነጠላ ለማህበሩ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

**አንቀጽ 17**

**የማህበሩ ኦዲተሮች**

1. የማህበሩ ኦዲተሮች በሕግ፣ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸውን ስልጣን በተግባር ያውላሉ።

2. የማህበሩ ኦዲተሮች የንብረትን፣ የሂሣብ ሚዛንን እንዲሁም የኪሳራ እና ትርፍ ሂሳቡን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስልጣን አላቸው። ሥራቸውንም ሲያከናውኑ አስፈላጊ ነው ብለው የሚያምኑበትን መዝገቦች፣ ቃለ-ጉባዔዎች እንዲሁም ሌሎች ሰነዶችን አስቀርበው የመመርመር ስልጣን አላቸው።

**አንቀጽ 18**

**የማህበሩ የሂሳብ ዓመት**

1. የማህበሩ የሂሳብ ዓመት የሚጀምረው ከጀነዋሪ 1 ቀን ሆኖ የሚያልቀው ዲሴምበር 31 ቀን ነው።

2. የመጀመሪያው የማህበሩ የሂሳብ ዓመት መቁጠር የሚጀምረው ከተመዘገበበት ቀንና ወር ጀምሮ ይሆናል።

**አንቀጽ 19**

**ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ**

ከማህበሩ ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ 10% (አሥር በመቶ) ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ የሚገባ ሲሆን ይኸውም የማህበሩ ካፒታል 20% (ሃያ በመቶ) እስኪሞላ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል። ይህ የመጠባበቂያ ተቀማጭ ከተሟላ በኋላ የኩባንያው ትርፍ በሙሉ ተመልሶ ለኩባንያው ሥራ እንዲውል ይደረጋል።

**አንቀጽ 20**

**የብድር ፖሊሲ**

1. ተቋሙ ብድር የሚሰጠው በምርታማ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ወይም ሊሰማሩ ለሚፈልጉ ሲሆን ዘላቂነትና አስተማማኝነቱ እየተገመገመ፣ እንዲሁም የተበዳሪዎች ብድሩን መልሶ የመክፈል አቅም ተጣርቶ ማህበሩ የሚመለከተው አካል ሲያፀድቅ ይሆናል።

2. ብድሩ ለቡድኖች ወይም ለግለሰቦች የሚሰጠው በማህበሩ የብድር ፖሊሲና ሥርዓት መሰረት ይሆናል።

3. ለተበዳሪዎች የሚሰጠው የብድር ጣሪያ በማህበሩ ቦርድ ይወሰናል። ሆኖም ይህ የብድር ጣሪያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከወሰነው የብድር ጣሪያ ሊበልጥ አይችልም።

4. ለሴቶች ልዩ ትኩረት መስጠት የተቋሙ የብድር ፖሊሲ አካል ይሆናል።

## አንቀጽ 21

### የማህበሩ መፍረስ

1. ማህበሩ የሚፈርሰው፤

    ሀ) የማህበሩ ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ ግባቸውን መትተዋል ተብለው በጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን፤

    ለ) በማንኛውም ሌላ ምክንያት ማህበሩ መፍረስ አለበት ብሎ የጠቅላላ ጉባኤ 3/4ኛ አባላት ሲወስኑ፤

    ሐ) አግባብ ያለው የሀገሪቱ ሕግ ሲወስን ይሆናል።

2. ማህበሩ ሲፈርስ ሂሳብ አጣሪዎች በቦርዱ ይሾማሉ። የሂሳብ አጣሪዎቹ ሙሉ የንብረት ቆጠራ ያደርጋሉ የማህበሩን ተበዳሪዎችና አበዳሪዎች ንብረትና ዕዳ ይመዘግባሉ፤ እንዲሁም በቦርዱ የተወሰኑትን ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናሉ።

3. የማህበሩ ንብረት ዕዳውን እንዲሸፍን የሚደረግ ሲሆን ዕዳውን ሸፍኖ የሚተርፍ ለአባላት አይከፋፈልም። ይልቁንም በጠቅላላ ጉባኤው በተወሰነው መሰረት ተመሳሳይ ተግባር ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች በስጦታ የሚሰጥ ይሆናል።

## አንቀጽ 22

### ማሻሻያዎች

1. በመመስረቻ ጽሑፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የሚደረገው ማንኛውም ማሻሻያ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አማካይነት ይሆናል።

2. የአስቸኳይ ጉባኤው የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓትና የምልዐተ ጉባዔ ጉዳይ የሚፈፀመው በንግድ ሕጉ ቁጥር 425 መሰረት ይሆናል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት

የማህበሩ መስራች አባላት ይህንን የመተዳደሪያ ደንብ ዛሬ መጋቢት 28 ቀን 1991 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውስጥ አንብበን አጽድቀናል።

| ተ.ቁ | ባለአክስዮን | የተወካይ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | | 27/1/92 |
| 2. | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | | 02/02/92 |
| 3. | አቶ ኃ/ማርያም ኃ/መስቀል ባንተረሳሁ | አቶ ኃ/ማርያም ኃ/መስቀል ባንተረሳሁ | | 25/01/92 |
| 4. | አቶ ግርማ ባንቲወሰን አይነቱ | አቶ ግርማ ባንቲወሰን አይነቱ | | 04/02/92 |
| 5. | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | እቶ ጌታቸው ወርቁ ወልደማርያም | | 10-02-92 |
| 6. | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መኩተ | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መኩተ | | 25/1/92 |
| 7. | ወ/ሮ ለበሰች ፀጋ ባለህ | ወ/ሮ ለበሰች ፀጋ ባለህ | | 24/1/92 |
| 8. | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | | 24/1/92 |
| 9. | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | | 4/2/92 |
| 10. | አቶ ኃይሌ ከፈኔ ጆሮ | አቶ ኃይሌ ከፈኔ ጆሮ | | 4/2/92 |
| 11. | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | | 25/1/92 |
| 12. | አቶ መቲፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | | 24/1/92 |
| 13. | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ሰሚነው | | 24/01/92 |
| 14. | ሲ/ር መሰረት ሺፈራው ይብራሁ | ሲ/ር መሰረት ሺፈራው ይብራሁ | | 25/01/92 |
| 15. | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | | 25/01/92 |

በክልል 14 መስተዳድር
የወረዳ 3 ፋይናንስ ጽ/ቤት የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ
ማኅተም
የተከፈለበት ምክንያት
የገንዘቡ ልክ ብር 355—
በፊደል
ወይም ብር የሆነ ቴምብር ተለጥፏል
የደረሰኝ ቁጥር 475245
9/2 ቀን 1992 ዓ.ም.
የቴምብር ቀረጥ መብት አስፈጻሚ
ስም
ፊርማ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር
የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ቁጥር 382/40/92

በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል

ወር 09/02 ቀን 19 92 ዓ.ም

ደርጋ ቃደሰ
የውልና ማስረጃ ምዝገባ
ጽ/ቤት ኃላፊ